RAYA FOUNDATION for tomorrow

RAYA
FOUNDATION
for tomorrow

203 Lexington Avenue
East Lansdowne, PA 19050 USA

# ያስታውሱ!

*የ4ኛው ዙር የራያ ፍውንዴሽን ሜሪት ስኮላርሽፕ ማመልከቻ አሁን ተጀምሯል ።*

ለ2010 ዓ.ም የሜሪት ስኮላርሽፕ ማመልከቻ ላስገባችሁ ተማሪዎች በሙሉ ፋውንዴሽኑ ምስጋና ያቀርባል። አጠቃላይ 64 ማመልከቻዎች ሲደርሱን ከነዚህ ውስጥ 12 በትምህርታቸው የላቀ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች በፋውንዴሽኑ ተሸላሚ ሆነዋል።

የ2011 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የራያ ፋውንዴሽን የሜሪት ስኮላርሽፕ ማመልከቻ መጋቢት 4 ቀን 2010 ዓ.ም ይጀምራል። ፋውንዴሽኑ ሁሉም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች የስኮላርሽፕ ማመልከቻቸውን እስከ መጋቢት 30 ቀን 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲያስገቡ ያበረታታል።

በዚህ ዙር፣ በድምሩ 12 የስኮላርሽፕ ሽልማቶች (9ኛ ክፍል=3፣ 10ኛ ክፍል=3፣ 11ኛ ክፍል=3 እንዲሁም 12ኛ ክፍል=3) ይሰጣሉ። በእያንዳንዱ ክፍል፣ ቢያንስ አንዱ የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ በትምህርቷ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበች ሴት ተማሪ ትሆናለች።

## የሽልማቱ መጠን

ከ9ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች በሁለት ሴሚስተሮች የሚከፈል በድምሩ 4000(አራት ሺ) የኢትዮጵያ ብር ይሰጣል። ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ አንድ ጊዜ የሚሰጥ በድምሩ 4000(አራት ሺ) የኢትዮጵያ ብር ይሆናል።

## የስኮላርሽፕ ማመልከቻ መስፈርቶች

አመልካቾች፥

1. በቆቦ መሰናዶና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ መሆን ይኖርባቸዋል
2. በራያ ፋውንዴሽን የተቀመጠውን የሜሪት መስፈርት ማሟላት (ይህም አመልካች ተማሪዎች ከየክፍሎቻቸው 1ኛ፣ 2ኛ ወይም ደግሞ 3ኛ መውጣት) ይጠበቅባቸዋል
3. በማመልከቻ ቅጹ የተጠቀሰውን የገንዘብ ፍላጎት/አቅም መስፈርት ማሟላት አለባቸው

## እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

ከላይ የተጠቀሱትን የማመልከቻ መስፈርቶች የሚያሟሉ አመልካቾች የማመልከቻ ሰነዶችን ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር/ዳይሬክተር ቢሮ መውሰድ ይችላሉ። አመልካቾች የመጀመሪያ ሴምሲተር የትምህርት ትራንስክሪፕታቸውን ጨምሮ የተሟላ የማመልከቻ ሰነዳቸውን የራያ ፋውንዴሽን ኢ-ሜይል (rayafoundation2014@gmail.com) በመጠቀም ቀጥታ በኤሌክትሮኒክ መላክ ወይም ደግሞ በትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ቢሮ በኩል ማስገባት ይችላሉ።

## የማመልከቻ ጊዜ ገደብ

የመጨረሻው የማመልከቻ መቀበያ ቀን መጋቢት 30፣ 2010 ዓ.ም ነው። ወቅታዊ ለሆኑ መረጃዎችና በበለጠ ለመረዳት የፋውንዴሽኑን ድህረ ገፅ እና የፌስቡክ ገፅ ይጎብኙ።